# የፋኖ ራዕይ

(BY FANOWEDY SAMARA)

በጣም ጥቅት ቁጥር ያላቸው ጅቦች በኢትዮጵያ ምድር ከተፈጠሩ አንበሶችና ነብሮች መካከል አብረው ሲኖሩ ተመለከትኩኝ። እነዚህ ጅቦች ለበርካታ ዓመታት አንበሶችና ነብሮች መስለው ከአንበሶቹና ነበሮቹ ጋር አብረው ይኖሩ ነበር። አብረው መኖር ብቻ ሳይሆን ይባስ ብለውም ያልሆኑትን እንደሆኑ በማስመሰልና እውነተኛው ባህሪያቸውን በመደበቅ አንበሶችና ነብሮችን ለመምራት በቅተው ነበር።

የተወሰነ ርቀት አብረው ከተጓዙ በኋላ እነዚህ አንበሶችና ነብሮች በተባበረ ክንዳቸው የጠላታቸው አከርካሪ በማያሻማ አኳሃን ሰብረው የአገሪቱ ወሳኝ ሃይሎች መሆን ከጀመሩ ወዲህ ግን የጀቦቹ ማንነት እየጎላ መጣና አንበሳና ነብር መሰሎ መኖር እንደማቻል ተገነዘቡ።

ጅባዊ እምነታቸውንና ፍላጎታቸው እውን ለማድረግም በጠራራው ፀሐይ መጮህ ጀመሩ። መጮህ ብቻም ሳይሆን ትክክለኛ አንበሶችና ነብሮች እኛ ነን፤ እናንተ ግን ጅቦች ናችሁ ብለው በጅባዊ አንደበታቸው አንበሶችና ነብሮችን መኮነን ተያያዙት።እውነት እላቸዋለሁ እነዚህ ጅቦች ያልሆኑትንና የሌላቸው ስብእና እንዳላቸው ተደርገው ለዘመናት የኖሩትም በአንበሶችና ነብሮች መካከል ተወሽቀው በመኖራቸው ብቻ ነው።

አሁን ከጥቅት ቀናት በኋላ ታይታ የማትጠገብ በ80 ቀለማት ያሸበረቀች አራተኛ ፀሓይ በመላ አገሪቱ ትወጣለች። ያቺ ፀሐይ ስትወጣ ጀቦች የሚኖሩበት የጨለማ ስፍራ እየጠበበ ይሄዳል። ምክንያቱም የጅቦች ኑሮ በጨለማና ጨለማን ተገን በማድረግ በመሆኑ ፀሓይዋን እንደወጣች ጅቦች የሚደበቁበት ቆሻሻ ስፍራ አየጠበበ ብሎም እየጠፋ ይሄዳል።

የጅቦች የመኖሪያ ስፍራ እየጠበበና እየጠፋ በሚሄድበት ጊዜ አንበሶች፣ ነብሮችና ሌሎች ከልብ የሚፈልጓትን ባለ 80 ቀለማት አራተኛ ፀሐይ ስትወጣ የመሬት ድምቀት ይጨምራል። ምስጥሩና ምክንያቱም እንደሚከተለው እነግራቸዋለሁ። በመጀመሪያ ደረጃ ፀሓይዋ እንደወጣች ወዲያው የመሬት ይዞታ ወርቅ በወርቅ ይሆናል። ይህን ከሁለት ዋናዋና ጉዳዮች የሚነሳ ሲሆን እነሱም አንድ የአንበሶችና ነብሮች አጥንት ወደ ወርቅ እየተቀየረ የሚሄድ በመሆኑ፣ ሁለት ደግሞ ህያው አንበሶችና ነብሮች ወርቅ ዘርተው ወርቅ የሚያፍሱ በመሆናቸው ነው። በሁለተኛ ደረጃም ሌሎች ሃይሎችም ቢሆኑ የአንበሶችና ነብሮች ትክክለኛ ማንነት በአግባቡ የሚገነዘቡበትና ትክክልኛ ወርቅ መሆናቸው የበለጠ እውቅና የሚሰጡበት ሁኔታ በጣም እየተቃረበ በመሆኑ ነው።

ይሁንና እነዚህ ወርቆች በቅርብም ሆነ በርቀት እንዳይታዩ ሌተቀን የሚለፉ ጀቦች አሉና ለአጭር ጊዜም ቢሆን ጅቦቹ በጅብኛ ሊያሰካኩ የሚችሉበት ዕድል በጣም

ጠባብ ቢሆንመ ፊፅሞ አይኖርም ግን አይባልም። እወነት ነው ጅብ በፀሐይ ሳይሆን በጨለማ የሚንቀሳቀስ በመሆኑ ፀሐይቱ ለጅቦች አትመችም።

ጊዜው መድረሱን የሚያሳይ አንድ ምልክት እነግራቸዋለሁ። እነዚህ ጅቦች ርሃባቸውና ጥማታቸው እየባሰ በሄደበት ቁጥር ድሮ አንበሶችና ነብሮች መሰለው በድብቅ ለኖሩበት ዘመን ከብዙ የጅቦች መንጋ በመሆን ከተፈጥሮአዊ ሂደት ወጥተው ያ ዘመን ተመልሰው በጅብኛ ይኮንኑታል። ከዚህ አልፈውም በሃወርያት አንበሶችና ነብሮች መቃብር ላይ ቆመው ሃወርያቱንና መቃብሩን ይወቅሳሉ። በዚያን ጊዜ ለተገኙ የአንበሶችና ነብሮች አንፃባራቂ ድሎች ለማንቋሸሽም በጅቦች ፊት ተንበርክከው በጅብኛ ይሰግዳሉ።

ልብ ያለው ያስተውል!! ይህ ምልክት ስታይ የጅቦች የመጨረሻ ዘመን ነውና እያንዳነዱ አንበሳ፣ ነብርና ሌሎችንም በአጠቃላይ በጥንቃቄ ጅቦችን ሊከታተልና ባለማቋረጥ ሊያጋልጣቸው ይገባል።

ጊዜው እየደረሰ ነውና የፀሐይቱ ድምቀትና ውበት የበለጠ እንዲጨምር የወርቁን መጠን ደግሞ በቀጣይነት እንዲያድግ ሁሉን አካል ራሱን ከጅብ መንጋ መጠበቅ እንዳለበት በጥብቅ እመክራለሁ!!